Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

MCPS የስራ ሁኔታ

ስለ አየር ሁኔታ መግለጫ እና ድንገተኛ ለውጦች ሲደረጉ ለቤተሰብ የሚሆን መመሪያ

ስለ ቀለም ኮዶች መግለጫ ይወቁ። መቼ መቃኘት እንዳለብዎት ይወቁ። የት መመልከት እንዳለብዎት ይወቁ።

ስለ ቀለም ኮዶች መግለጫ ይወቁ

አረንጓዴ

መደበኛ ሥራ ይካሄዳል
ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች በሠዓቱ ይከፈታሉ የህጻናት እንክብካቤ እና የማህበረሰብ አገልግሎት በተያዘው መርሃ ግብር መሠረት ይከናወናሉ።

ቢጫ

ትምሕርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዘግይተው ይከፈታሉ
ትምህርት ቤቶች፣ ቢሮዎች፣ እና የጠዋት አውቶቡሶች ሁለት ሰዓት ዘግይተው ሥራ ይጀምራሉ ወይም ይንቀሳቀሳሉ። ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን የሚያሰናብቱት በተለመደው ሰዓት ይሆናል። የህጻናት እንክብካቤ መርሐ ግብሮች (የጠዋት፣ የሙሉ ቀን፣ እና ከትምህርት ሰዓት በኋላ) በተያዘላቸው መርሐ ግብር መሰረት ሊሰሩ ይችላሉ፤ ቤተሰቦች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አገልግሎት ሰጪያቸውን ማነጋገር አለባቸው።

ሰማያዊ

ተማሪዎች ከመደበኛው ሰዓት ቀደምብሎ ይሰናበታሉ
ትምህርት ቤቶች በተገለጸው ሰዓት ይዘጋሉ። ከቀትር በኋላ እና ምሽት ላይ የሚከናወኑ የትምህርት ቤትና የማህበረሰብ አገልግሎቶች ዝግ ይሆናሉ። የህጻናት እንክብካቤ አገልግሎቶች መስራታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ፤ ቤተሰቦች የህጻናት እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪያቸውን ማነጋገር አለባቸው።

ብርቱካንማ

ትምህርት ቤቶች ዝግ ይሆናሉ / ቢሮዎች ክፍት ናቸው
ትምህርት ቤቶች ዝግ ይሆናሉ። ትምህርት ቤቶች እና ማዕከላዊ ቢሮዎች በሰዓቱ ይከፈታሉ። MCPS ስፖንሰር የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ተሰርዘዋል። የህጻናት እንክብካቤ አገልግሎቶች እንደተለመደው ሊቀጥሉ ይችላሉ፤ ቤተሰቦች የህጻናት እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪያቸውን እንዲያነጋግሩ ይመከራሉ።

ቀይ

የትምህርት ስርዓቱ ተዘግቷል ማለት ነው።
ትምህርት ቤቶችና ቢሮዎች ተዘግተዋል። ሁሉም እንቅስቃሴዎች፣ የህጻናት እንክብካቤ እና የማህበረሰብ አገልግሎቶች ተሰርዘዋል።

ሐምራዊ

በአንላይን ቨርቹዋል ትምህርት የሚሰጥበት ቀን
የትምህርት ቤት እና የቢሮ ህንጻዎች ዝግ ይሆናሉ፤ ሰራተኞች እና ተማሪዎች በአንላይን/ቨርቹዋል ሪፖርት ያደርጋሉ። ትምህርት የሚሰጠው በአንላይን ነው፤ ክፍሎች ከተለመደው/ከመደበኛው መርሐ ግብር በሁለት ሰዓት ዘግይተው ይጀምራሉ። ትምህርት ቤትዎ ተጨማሪ መረጃዎችን ይሰጥዎታል። ከትምህርት ሰዓት በፊት እና በኋላ የሚከናወኑ ፕሮግራሞች እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች ተሰርዘዋል።

ውሳኔዎች የሚወሰኑት እንዴት ነው?

ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። MCPS፤ የብሔራዊ የአየር ትንበያ አገልግሎት (National Weather Service) ትንበያዎችን፣ የመንገድ እና የትራፊክ ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም ከካውንቲው ምላሽ ሰጪ ኤጀንሲዎች እና ከሌሎች የአካባቢው የትምህርት ዲስትሪክቶች የሚወጡ መረጃዎችን ይገመግማል።

7 PM	5 AM	10:30 AM
በምሽት የሚተላለፍ ውሳኔ	በጠዋት የሚተላለፍ ውሳኔ	ተማሪዎችን ከወትሮው ቀድሞ ማሰናበት

የአየር ሁኔታ የከሰዓት በኋላ መጓጓዣን ሊያስተጓጉል በሚችልበት ጊዜ ተማሪዎችን ቀደም ብሎ ይሰናበታሉ።

ኦፊሴላዊ መረጃዎችን ያግኙ

MCPS ድረገጽ	www.montgomeryschoolsmd.org
ALERT MCPS / MCPS ALERTA	ይመዝገቡ፡-montgomeryschoolsmd.org/emergency/alertmcps
PARENTSQUARE ALERT	ስለ ParentSquare የበለጠ ይወቁ እና QR ኮድ ላይ ይመዝገቡ።
በማህበራዊ ሚድያ	X: @mcps | Facebook: @mcpsmd | Instagram: @mcps_md
የትምህርት ቤት ድረገጽ	የትምህርት ቤትዎን የመረጃ ድረ ገጽ ይመልከቱ
MCPS የአደጋ ጊዜ የስልክ መስመር	በዚህ የስልክ ቁጥር ይደውሉ (240) 740-3010 (እንግሊዝኛ/English /ስፓንሽኛ/ español)

ሙሉ ዝርዝር እና የፕሮግራም ልዩ ሁኔታዎች፡montgomeryschoolsmd.org/emergency/closings